# ጊዜው ሲደርስ !!!



እንኳን አንድ መለስ፥ ያውም ቀትረ - ቀላል፣
ጎልያድ በወንጭፍ ተዘርሮ ወድቋል !
ታላቁ ናፖሊዎን ሽምቆ ኮስምኗል !
ሂትለር ባለግርማው ባፍጢሙ ተደፍቷል !
ዱቼ ሙሶሎኒ ዘቅዝቆ ተሰቅሏል !....
ኢዲ አሚን፥ ሞቡቱ ...
ዚያድባሬ፥ መንግሥቱ ...
ሲለበልባቸው እሣቱ፣
የሕዝብ ኃይል ትኩሳቱ፤
እግሬ አውጪኝ ፈርጥጠዋል፣
በስደት ቃጠሎ ነደዋል።
እንኳንስ ምርኮኛ - በረከት ብአዴን...
እንኳንስ ምርኮኛ - አባዱላ ኦህዴድ...
እንኳንስ ወያኔ የመለስ ኢህአዴግ...
ፋሺዝም፥ ናዚዝም ተንኮታኩቶ ወድቋል፣
የደቡብ አፍሪካ ባንቱስታ ተንዷል፣
የአፓርታይድ ሠይጣን ተገርስሶ ተኗል፣
የሶቭየት ሕብረት ብትንትኗ ወጥቷል፣
ደርግና ኢሠፓ ተሸማቆ ሟምቷል።
እንኳንስ «አግአዚ» የሕወሃት ሚሊሽያ፣
በዘር የታጀለው ጠባብ ማስፈራሪያ፤
ዓለም ያሸበረው የናዚም ጦር ሟሸዋል፣
ሕዝብን የለያየው የጀርመን ግንብ ፈርሷል...
ተገኝቷል በዓለም የማይመስለው ሆኖ፣
ያላለሙት ራዕይ በተዐምር ሰፍኖ !!!።
ሁሉም ጊዜው ሲደርስ፣
ጽዋው ሞልቶ ሲፈስ፤
በስተመጨረሻ የዕውነት ማዕበል፣
ዘረኛውን ሁላ ይጠራርገዋል !!! ።

ጌታቸው አበራ